# ADDA BILISUMMAA OROMOO

**OROMO LIBERATION FRONT**

**مورو أ ريرحتة هبج□و**

Gaafa: 13-02-2012 خيراتل
Date:

Lakk.: 003/stm-abo/2012 مقر
No.:


## *በኦሮምያ የተጀመረው የአንገዛም ባይነት ኣመፅ የወያኔን ስርኣት ከነስሩ መንግሎ እስከሚጥል ድረስ ተጠናክሮ ይቀጥላል*

## *የኦሮሞ ነፃነት ግንባር መግለጫ*

የወጣቶች ንቅናቄ ለነፃነትና ለዴሞክራሲ (ቄሮ) እና የኦሮሞ ህዝብ ኣብዮት ኣስተባባሪ ጉባኤ ባለፈው ጥር ወር ውስጥ -ረ ወያኔ ኣመፅ በጋራ ማወጃቸው ይታወቃል። የኣዋጁን መግለጫ ተከ ትሎም የኦሮሞ ህዝብ በተለይም ወጣቱ ትውልድ (ቄሮው) የተያያዙት የኣንገዛም ባይነት ኣመፅ በተለያዩ የኦሮምያ ኣካባቢዎች ተፋፍሞ ወደ ከፍተ ደረጃ በመሸጋገር ላይ ይገ ል። የኦሮሞን ህዝብ የመብት ጥያቄ በሰላማዊ መንገድ ለማቅረብ የተጀመረው ይህ የኣመፅ እንቅስቃሴ ሰላማዊ ሰልፎችን ማካሄድም የሚጨምር ነው። የወያኔ መንግስት ግን ህዝቡ በሰላማዊ መንገድ ለሚያቀርበው የመብት ጥያቄ ሰላማዊ ምላሽ በመስጠት ፋንታ እንደልማዱ የፖሊስና የጦር ሃይሉን ኣሰማርቶ ኣሙን ለማፈን ጥረት ላይ ይገ ል። ለዚህ ሰላማዊ ጥያቄ ከመንግስት የሚ ሰጠው ምላሽ እስራት፣ ድብደባ፣ ኣፈና፣ ከትምህርትና ከስራ ገበታ መባረር የመሳሰሉት እርምጃዎችን መውሰድ ሆኖኣል።

በዚህ የኣፈናና የማስፈራሪያ እርምጃ መዳፍ ስርም ቢሆን የኦሮሞ ልጆች የጀመሩት የኣንገዛም ባይነት ኣመፅ ይበልጥ እየተስፋፋ ይገ ል እንጂ የሁዋልዮሽ ኣልተመለሰም። ከኦሮምያ የተለያዩ ኣካባቢዎች የሚወጡ ሪፖርቶች እንደሚጠቁሙት በቄሮው የኦሮሞ ወጣት የተጀመረው ይህ ህዝባዊ ኣብዮት ኣድማሱን በይበልጥ እያሰፋ ወደ ኣዲስ ምእራፍ በመሸጋገር ላይ ነው። በተለይም በሃገሪቷ በሚገ -ት ሁሉም ከፍተ የትምህርት ተቋዋማት በሚማሩ የኦሮሞ ወጣቶች ዘንድ የተጀመረው የኣንገዛም ባይነት ኣመፅ በቀላሉ የሚዳፈን ኣልሆነም። ኣንዳንድ የቅርብ ጊዜ ምሳሌዎችን ለመጥቀስ ያህል በጅማ ዩንቨርሲቲና በኣዳማ ዩኒቨርሲቲ የተቀጣጠለው የተማሪዎች ኣመፅ በመካረሩ የወያኔ መንግስት ሁለቱንም ዩኒቨርሲቲዎች በፖሊስ ሃይሉ ኣስከብቦ ለማስጠበቅ ተገዷል። እንዲያውም በጅማ ዩኒቨርሲቲ የተማሪዎቹ እምቢ ለጭቆና ኣመፅ ከወያኔ መለዮ ለባሾች ቁጥጥር ውጭ ከመውጣቱም ባሻገር ሁለት በዩኒቨርሲቲው የተሰገሰጉ የስርኣቱ ሰላዮችን እስከመቅጣት ደርሷል። በሃረማያ ዩኒቨርሲቲም ተመሳሳይ የፀረ ጭቆና ኣመፅ በተማሪዎች እየ ተካሄደ መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ። በተቀሩት የሃገሪቷ ዩኒቨርሲቲዎችም የተጀመረው ኣ መፅ ኣንዱ ከሌላ ው ጋር እየተያያዘ የፀረ ጭቆና ትግሉን ኣድማስ በማስፋት ላይ ይገ ል።

በምዕራብ ሸዋ የካቺሲ ከተማ ትምህርት ቤቶች መምህራን በቄሮው የኦሮሞ ወጣት ወደተቀጣጠለው ኣመፅ በመቀላቀል የኣንገዛም ባይነት ድምፃቸውን እያሰሙ ናቸው። መምህራኑ በኣባይ ግድብ ስም ከደመወዛችን የሚቆረጠው ገንዘብ ይመለስልን የሚል ጥያቄም ኣንስተዋል። ጥያቄያቸው ፍትሃዊ ምላሽ እስከሚያገ ድረስም የመማር ማስተማሩን ስራ ኣቁዋርጠው ወደ ህዝባዊው ኣመፅ ተቀላቅለዋል። የትምህርት ቤቶቹ ተማሪዎችም የመምህራኖቻችን ጥያቄ የ ም ጥያቄ ነው ሲሉ ድጋፋቸውን ገልዋል። የከተማዋና ኣካባቢው የኦሮሞ ወጣቶች በኣርሶ ኣደሩና በነጋዴው ላይ የተጣለው ግብርና መውጮ ኢ-ፍትሃዊ በመሆኑ ባስቸኩዋይ መቆም ኣለበት ሲሉ የኦሮምያ ትምህርት ቢሮ የጠራውን ስብሰባ ኣስበትነዋል። በምስራቅ ኦሮምያ ጭሮ ከተማም የ ኦሮሞ ተማሪዎች የተያያዙት ኣመፅ የከተማዋን የወያኔ ካድሬዎሸች ኣጣብቂ ውስጥ ከቷል።

በተለያዩ የኦሮምያ ኣካባቢዎች በስርኣቱ ካድሬዎች ተታልለው የኦፒዲኦ ኣባልነት የ ተቀበሉ የኦሮሞ ተማሪዎች ባሁኑ ጊዜ ስማቸውን ከቆሻሻው የጠላት መዝገብ በመፋቅ ወደተቀደሰው የረ ጭቆና ኣመፅ መቀላቀላቸው በወያኔ መንግስት ላይ ተጨማሪ የእግር እሳት ሆኖበታል።

ከዚሁ ህዝባዊ ኣመፅ ጋር በተያያዘ በማዕከላዊ ኦሮምያ ጊንጪና ግንደበረት ከተሞችን የሚያገና ው መንገድ በኣካባቢው ህዝብ እርምጃ ተዘግቷል። መንገዱ ለነዋሪው ህዝብ ከሚሰጠው ፋይዳ ይልቅ ወያኔና ሸሪኮቹ ባለሃብቶች የዝርፊያ እንቅስቃሴያቸውን እን ዲያቀላጥፉ እያገለገለ መሆኑ ነው የተደረሰበት። የወያኔ ፖሊስ ሃይል በድንጋይና በእንጨት ግንዶች የተዘጋውን መንገድ ለጊዜውም ቢሆን መልሶ ለትራፊክ ክፍት እን ዲያደርግ ከበላይ ኣዛዥ ግዳጅ ተሰጥቶታል። ኣሁን መንገድ የመዝጋት ደረጃ ላይ የ ደረሰው የህዝቡ ኣንገዛም ባይነት ኣመፅ ወደ ሌሎች ከፍተ  እርምጃዎችም መሸጋገር ጀምሯል። በዚሁም መሰረት በኢሉ ኣባቦራ ዞን በደሌ ወረዳ ኣለባሽ በተባለች የገጠር ቀበሌ የሚገ ውና ንብረትነቱ ኣብዱል መጂድ የተባለ የኣንድ ፓኪስታናዊ ባለሃብት የ ሆነው 15,000 ሄክታር የሚሆን የሸንኮራ ኣገዳ ማሳ ሙሉ በሙሉ በእሳት መውደሙ ለዚህ እውነታ ኣንድ ምሳሌ ሊሆን የሚችል ነው። ለሸንኮራ ኣገዳ ምርት ተብሎ ለዚህ የውጭ ኢንቬስተር የተሰጠው መሬት ቀደም ሲል መሬቱን ኣርሰው የሚተዳደሩበትን 1,200 የሚሆኑ ነባር የኦሮሞ ነዋሪዎችን በሃይል በማፈናቀል የተወሰደ መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ። ይህ የሸንኮራ ኣገዳ ማሳ "ኣል ሃበሽ" ለተባለው የስኩዋር ፋ- በሪካ ጥሬ ምርት እንዲያቀርብ ከመንግስት ጋር ስምምነት (joint venture) ላይ ተደርሶ እየተሰራበት እንደነበረ ይታወቃል።

ከመሬቱ ላይ የተፈናቀለው ነዋሪ ህዝብ ለኣቅራቢያው የመንግስት ኣስተዳደር ኣካላት በተደጋጋሚ ቢያመለክትም የተሰጠው ምላሽ "ከፈለጋችሁ መሬቱን ለወሰደው ኢንቬስ ተር በጉልበት ስራ ኣገልግላችሁ መኖር ትችላላችሁ፤ ነገር ግን መሬቱ ይመለስልን የ ማለት መብት የላችሁም" የሚል ነበር። በተለያዩ የኦሮምያ ኣካባቢዎች በጭቁዋ - መን ግስት ህዝብ ላይ የሚወሰደው የዘረፋና የግፍ እርምጃ ስፍር ቁጥር የለውም። በሃይል ከቀዬው የሚፈናቀለው ዜጋ ብሶቱን ከሚያመለክትበት ኣካል ፍትሃዊ ምላሽ ሲያጣ ን ብረቱን ወደመከላከል እርምጃ መግባቱ የማይቀር ነው። በዚህ ሳቢያ ደግሞ ለሚከተለው ሰብኣዊና ኣደጋና ኢኮኖሚያዊ ውድመት ተጠያቂ የሚሆነው ለህዝብ ጥያቄ ጆሮ ዳባ ያለው የወያኔ መንግስት ይሆናል።

በተመስሳይ ሁኔታ ሊ ኪንግ ሻንግ የተባለ ከወያኔ ጋር ተሻርኮ ህዝብን በመበደል ተግባር ላይ የተሰማራ የቻይና ባለሃብት በምዕራብ ሸዋ ኣደኣ በርጋ ወረዳ ሬንጂ በተሰ ች ከተማ ላይ የካቲት 7, 2012 ከህዝባዊ ኣሙ ጋር በተያያዘ መገደሉ ተዘግቧል። ከደንገቴ ሲሚንቶ ፋብሪካ ከፍተ ውን የኣክሲዮን ድርሻ የያዘው ይህ የ ቻይና ባለሃብት መገደሉ የተሰማው ፋብሪካው የተገነባበት መሬት ባለቤት የሆነው ነዋሪ ህዝብ በግፍ ከቀዬው መፈናቀሉን ተከትሎ ነው። ቻይናዊው ባለብሃት የወያኔን መን ግስት መከታ በማድረግ ለባለመሬቱ ዜጋ ከፍተ  ንቀት በማሳየት ይታወቅ እንደነበርና ይህም ብዙዎችን ያስቆጣ መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ። ከቀዬው በሃይል የ ተፈናቀለው ነዋሪ ህዝብ ተገቢው ካሳ እንዲከፈልለት በተደጋጋሚ ቢያመለክትም ሰሚ ጆሮ ማጣቱን ተከትሎ ይህ እርምጃ መሰማቱ የኦሮሞ ህዝብ ለዘራፊው የወያኔ መንግስ ት ያለው ትዕግስት እየተሟጠጠ መሆኑን ኣመላካች ነው። እንዲህ ኣይነቱ ሁኔታ ከ

መከሰቱ ኣስቀድሞ ገንዘባቸውን በተሳሳተ መልኩ ኢንቬስት ለሚያደርጉ ባለሃብቶች ኦ ነግ በቂ ማሳሰቢያና ምክር መለገሱ የሚታወስ ነው። ለኦነግ ምክርና ማሳሰቢያ ጆሮ ዳባ ማለት ለዚህ ኣይነቱ ኣደጋ እንደሚያጋልጥ መገንዘብ ጠቃሚ ነው። ወደፊትም ተመሳሳይ ሁኔታዎች በስፋት መከሰታቸው እንደማይቀር ኣያጠያይቅም።

ዛሬ በኦሮምያ በገዛ ሃገራቸው ላይ የተገፉ ዜጎች ብሶታቸውን የሚያመልክቱበት ኣካል በማጣታቸው እምባቸው ኣልቆ ደም እያነቡ ናቸው። ስለሆነም ኣሁን የሚሰማው ኣይ ነት ጭቁዋኖችን የሚቀጣ ህዝባዊ እርምጃ በተቀሩትም ኣካባቢዎች በስፋት ከተከሰተ የ ሚያስገርም ሊሆን ኣይችልም። ባሁኑ ጊዜ በኦሮምያ መሬት ብቻ ሳይሆን የደን ሃብትም በስፋት እየወደመ ነው። ለኣብነት ያህል ምዕራብ ሸዋ ውስጥ የሚገ ው የ ጭሊሞ ደን በገፍ እየተመነጠረ ወዳልታወቀ ስፍራ እየተጫነ ይገ ል። ለተፈጥሮ ኣ ካባቢ እንክብካቤና ውበት ከፍተ  ድርሻ እንዳለው የሚታወቀው ይህ ደን ተመንጥሮ ወደ ምድረ በዳነት መቀየሩ ለኦሮምያ መፃኢ እድል ኣሳሳቢ ነው። በዚህ ሳቢያ ወደፊት የሚከተለው ኣደጋ የከፋ መሆኑን ኣስቀድመው የተረዱ የህዝብ ልጆች ስ ጋታቸውን ለሚመለከተው የመንግስት ኣካል በተደጋጋሚ ቢያመለክቱም ተገቢ ምላሽ ኣ ልተሰጣቸውም። የህዝብን ብሶትና ጥያቄ በሰላማዊ መንገድ ማስተናገድ ያልፈለገው ወያኔ ከላይ የተጠቀሰው ኣይነት ሕዝባዊ እርምጃ ከተወሰደ በሁዋላ መደንበሩ ምንም ዋጋ ኣይኖረውም። ለእርምጃው ተጠያቂ የሚያደርጋቸውን ሰላማዊ ዜጎች ኣፍሶ ማሰርና ማስፈራራትም መፍትሄ ሊሆን ኣይችልም። መፍትሄ የሚሆነው ህዝብ ኣምርሮ የመ ሰለውን ራስን የመከላከል እርምጃ ወደ መውሰድ ከመግባቱ ኣስቀድሞ በሰላማዊ መን ገድ ለቀረበው ህዝባዊ ጥያቄ ሰላማዊና ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት መዘጋጀት ብቻ ይሆናል።

የኦሮሞ ህዝብ በልጆቹ ፋና ወጊነት ይዞ የተነሳውን ሰላማዊ የመብት ጥያቄ ኦነግ የ ሚደግፍ መሆኑን ዳግም ያረጋግጣል። ለዚህ ሰላማዊ ጥያቄ ሰላማዊ ምላሽ እንዲሰጥም ምኞቱ ነው። ይሁን እንጂ የወያኔ መንግስት እንደ ልማዱ ለቀረበለት ሰላማዊ የህዝብ ጥያቄ የሃይልን እርምጃ እንደ ምላሽ መጠቀምን መርጧል። የኦሮሞ ህዝብ ለዚህ ኣ ምባገነናዊ ስርኣት የሃይል እርምጃ ከቶ ሳይንበረከክ መብቱን ለማስከበር የጀመረውን ሰላማዊ ትግል ይበልጥ እንዲያፋፍም ኦነግ የበኩሉን ጥሪ ያስተላልፋል። እን ደማናቸውም የኣለማችን ኣምባገነን ስርኣቶች ሁሉ የወያኔ መንግስትም የህዝብን ሰላማዊ የኣብዮት እንቅስቃሴ ሌላ መልክ ሰጥቶት ለመምታት እንዲያመቸው የተቻለለትን ሴራ ሁሉ ከመሸረብ እንደማይቆጠብ መታወቅ ኣለበት። የኦሮሞ ህዝብ በበኩሉ በጠላት ሊሸረቡ የሚችሉ ማናቸውንም ኣይነት ሴራዎች ኣስቀድሞ ደርሶበት በማጋለጥ ኣ ብዮታዊ እንቅስቃሴውን ይበልጥ በረቀቀና በተደራጀ መልኩ ኣፋፍሞ የወያኔን መንግስ ት መፈናፈ  ማሳጣት ይጠበቅበታል። የተጨቆነ ህዝብ ለመብቱ መከበር የሚያደርገው ትግል የማታ ማታ ድል መጎናፉ ኣይቀሬ ነው። የኦሮሞ ህዝብ ኣንገዛም ባይነት ኣ መፅም የወያኔን ስርኣት ከነስሩ መንግሎ እስከሚጥል ድረስ ተጠናክሮ ይቀጥላል!

**ድል ለኦሮሞ ህዝብ!**

**የኦሮሞ ነፃነት ግንባር**

**የካቲት 13, 2012**